# የልጆች ፀሎት ቃልኪዳን

**ፀጋ** በሰማይ ያለህ አባቴ ሆይ
ከልጆችህ አንዷ/ዱ ስላደረከኝ
አመሠግንሃለሁ፡፡

**ፍቅር** እንድወድህ እና እንድታዘዝህ
እርዳኝ፡፡

**ርሕራሔ** አንተ እንደምትወደኝ ሌሎችን
እንድወድ እርዳኝ፡፡

**ንስሃ** ስለሃጢያቴ ይቅርታ አድርግልኝ
ንፁህ አድርገህ እጠበኝ፡፡

**አምልኮ** በሙሉ ልቤ አመሠግንሃለሁ!

**መሰጠት** ኢየሱስ ጌታዬ አድርጌ ልከተልህ
እፈልጋለሁ፡፡

**መደገፍ** በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ፡፡

**ተጽኖ** የእውነት፣ ፍትህ፣ እና ፀጋህ
መሣሪያ አድርገኝ፡፡

**ደቀመዝሙርነት** ሌሎችን ወደ አንተ ለመጋበዝና
ለክብርህ ተጠቀምብኝ

**ስልጣን** በኢየሱስ ስም ፀለይኩ አሜን

# የቃል ጥናት ጥቅሶች

**የጠፋው በግ ታሪክ · ሉቃስ 15:1-7** | የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። — 1ኛ ዮሐንስ 3:1

**የአብርሃም ታሪክ · ዘፍጥረት 12:1-5** | ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። — ማቴ22፤37፤38

**ደጉ ሣምራዊ · ሉቃስ 10:25-37** | እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። — ዮሐንስ 15:12

**ይቅርታ ያላደረገው ባሪያ ምሣሌ · ማቲዎስ 18:21-35** | ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ። — መዝሙረ ዳዊት 51:2

**የጌታ ልደት ታሪክ · ሉቃስ 2:1-20** | አቤቱ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥ ተአምራትህንም ሁሉ እነግራለሁ። — መዝሙረ ዳዊት 9:1

**ጴጥሮስ ፍፁም አልነበረም · ሉቃስ 22:54-62** | እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። — ዮሐንስ 13:13

**አጽናኙ · ዮሐንስ 14:15-31** | መንፈስ ይሙላባችሁ — ኤፌሶን 5:18ሀ

**ኢየሱስ እና ልጆች · ማቲዎስ 18:1-6** | ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። — ዮሐንስ 1:14

**የጠርሴሱ ሳውል ጳውሎስ ሆነ · ሐዋ 9:1-22** | እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ — ማቲዎስ 28:19

**አይነ ስውሩ በርጤሜዎስ · ማርቆስ 10:46-52** | በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ — ፊሊጲሲዮስ 2:9

40 DAY PRAYER COVENANT For Kids! | 4/14 window movement | YouVersion | (+228) 90 19 36 46

©2014 The 40 Day Prayer Covenant Inc. All rights reserved